# የዕጽዋት ዘር ረቂቅ አዋጅ

## ዋና ዋና ለውጦች ላይ ትኩረት በመስጠት የቀረበ ማብራርያ

የካቲት 23 2014
ግብርና ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

## መግቢያ

በመደበኛ መልኩ የዘር ማምረትና ሥርጭት ሥራ መስራት የተጀመረው የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ኮርፖሬሽን በ1970ቹ ተደራጅቶ ሥራ መስራት ከጀመረ በኃላ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኃላ ፓዮኒር ሃይብሪድ በጆይንት ቬንቸር ከኮርፖሬሽኑ ጋር ሲሰራ ቆይቶ በ1990ቹ የሁለቱም የጋራ ስራ ተቋርጦ ፓዮኒር ራሱን ችሎ መስራት ጀመረ። አገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደነገገ አዋጅ ኖሯት መስራት የተጀመረው እነዚህ ሁለት ኩባንያዎችና በነበሩበት በ1992 ዓ/ም አዋጅ ቁጥር 206/1992 መሰረት ነው። ይህ አዋጅ ሥልጣን ባብላጫው የሰጠው ለፌደራል ግብርና ሚኒስቴር ሲሆን የክልሎች ሥልጣን ያላገናዘበ አንደነበር ተግባራዊ መሆን በጀመረበት ወቅት አስመስክሯል። ይህን ችግር ለመፍታትና የፌደራልና የክልል ሥልጣንን በግልጽ ለይቶ ለማስቀመጥ በማሰብ እንዲሁም በዘር ኢንድስቱሪው እየታየ የመጣውን አገራዊ እና ዓለም አቀፍ ዕድገቶች መሰረት በማድረግ አዋጅ ቁጥር 206/1992 ተሽሮ በአዋጅ  ቁጥር 782/2005 አንዲተካ ተደረጓል። ይህ አዋጅ በዋናነት የክልል እና የፌደራል ሥልጣንን በግልጽ ያስቀመጠ ስለነበር በአተገባበሩ ከመጀመሪያው አዋጅ የበለጠ አፈጻጸም ነበረው።

## አዋጅ ቁጥር 782/2005 በመሻር አዲስ የዘር አዋጅ ማውጣት ለምን አስፈለገ?

አዋጅ ቁጥር 782/2005 አገራዊ አፈጻጸሙ ከአዋጅ ቁጥር 206/1992 አንጻር የበለጠ ቢሆንም በዘር ዘርፉ የውጭ ኢንቨስትመንት ከማበረታታት አንጻር፣ አገሪቱ የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር፣ በዕጽዋት ዘር የውጭ ንግድን ተሳፎ ከማሳደግ አኳያ፣ በልዩ ሁኔታ ከውጭ የሚገቡ የዕጽዋት ዝርያዎች ሳይመዘገቡ ወደ ምርት የሚገቡበት ሁኔታን በማካተት እያደገ የመጣውን የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ከመደገፍ ረገድ፣ በውል ላይ ተመስርቶ ዘር በአርሶአደር ማሳ ስለማባዛት እና ለዘር አምራች ድርጅቶች እውቅና በመስጠት የውጭ ኢንቨስትመንት ከማበረታታት አኳያ፣በገበያ ውድድር መርሆዎች ላይ የተመሰረተ የግብይት ስርዓትን ስለማስፈን፣ ስለ መጠባበቂያ የዘር ሥርዓት የመዘርጋት አስፈላጊነት፣ በዘር ጥራት አገልግሎት አሰጣጥ ዘር አምራቾች እና የግልና የመንግስት ተቋማትን በማሳተፍ የመንግስትን ወጪ ስለመቀነስና እና ሌሎችንም አስመልክቶ ያላከተተ ወይም ግልጽነት የጎደለው እንደ ሆነ በሴክተሩ መሳተፍ የሚፈልጉ የውጭ ኩባንያዎች ከሚያቀርቡት ሪፖርት፣ በአተገባበር ሂደት ካጋጣሙ መሰናክሎች እና በተለያዩ መድረኮች ከሚንጸባረቁ አስተያየቶች ስለተረጋገጠ እነዚህን በማካተት የህግ ክፍተቱን ለመሙላት ይህን አዋጅ በአዲስ ረቂቅ አዋጅ መተካት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ለረቂቅ አዋጁ ዝግጅት መነሻ ሌላው ምክንያት ደግሞ የዕጽዋት ዘር ፖሊሲው ነው። ሚኒስቴሩ በቅርብ ጊዜ አርቅቆ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ካቀረበው የዕጽዋት ዘር ፖሊሲ አንጻር እና በአገሪቱ እየታየ ካለው አጠቃላይ የመንግስት ሪፎረም አኳያ የህግ ማዕቀፎች እንዲጣጣሙ ከተሰጠው የመንግስት አቅጣጫ አንጻር ነባር የዕጽዋት አዋጁ እንዲሻሻል እንደገና በአዲስ መልኩ በማቅረብ ማጸደቅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በአዲስ መልኩ እንዲሆን የተፈለገበት ሁኔታ በዋናነት አዳዲስ ድንጋጌዎች በስፋት የተካተቱ መሆኑ እና ነባሮቹም ቢሆን በይዘትም ሆነ በቅርጽ ጉልህ ለውጥ የተደረገባቸው በመሆኑ ነው።

## ረቂቅ ህጉን በፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማጸደቅ ለምን አስፈለገ?

የእጽዋት ዘር በዋናነት ድንበር ተሸጋሪ ግብዓት መሆኑ ግልጽ ነው። ድንበር ተሸጋሪነቱ አገር አቀፍ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍም ይዘት ያለው ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ እስከአሁን በነበረው የመደበኛ የዘር ሥርዓቱ የሰባት አሰርት ዓመታት ታረክ ውስጥ የአቅርቦቱ ድርሻ ይመራ የነበረው በፌደራል ደረጃ በተመዘገቡ የዕጽዋት ዘር ኩባንያዎች ነበር። ክልሎች የራሳቸውን የዘር አምራች ድርጅቶች ማቋቋም ከጀመሩበት ካለፉት አስር ዓመታት ወዲህ ግን የፌደራሉ ድርሻ ቀስ በቀስ በክልሎች ድርሻ እየተወሰደ በመምጣቱ በፌደራል ይመራ የነበረው አሰራር ክልላዊ ይዘትም አንዲኖረው ሆኗል። በአንድ ክልል የሚመረት ዘር በማናቸውም መልኩ ወደ ሌላ ክልል ገብቶ ጥቅም ላይ መዋሉ የማይቀር መሆኑን ግልጽ ነው። ስለዚህ ዘር ከማዕከል ብቻ ሳይሆን ከክልል ወደ ክልልም

ለግብይት ይውላል። ይህም ብቻ ሳይሆን የዕጽዋት ዘር በዋናንትም የአትክልት ዘር ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ የሚገባው ከውጭ አገሮች ነው። ከቅርብ ግዜ ወዲህም የምግብ ሰብሎች ምርጥ ዘር ከአፍሪካ አገሮች መግባት ጀምሯል። ይህን አገር ተሻጋሪ ግብዓት ደግሞ በዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶች መሰረት ማሳተዳደርን ይጠይቃል። ይህ የሚያሳየን ዘር አገር አቀፍም ዓለም አቀፍም ይዘት እንዳለው ነው። ስለዚህ በዕጽዋት ዘርፍ የፌደራሉ ድረሻ የጎላ መሆኑን እንመለከታለን።

በዕጽዋት ዘር ትኩረት ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች አንዱ ደግሞ ጥራትን ማረጋገጥ ነው። ጥራትን ማረጋገጥ በዋናነት ከስታዳርዳይዜሽን ጋር የተቀራኘ ነው። ስታዳርዳይዜሽን ደግሞ በህገመንግስቱ የፌደራል ሥልጣን መሆኑ በግልጽ የተቀመጠ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ከውጭ የሚገባም ሆነ ወደ ውጭ የሚላክን ዘር ጥራት ማረጋገጥና መቆጣጠር ተገቢነትን ያሳየናል። ይህም የፌደራሉን ድርሻ የሚያጎላ ነው።

ከብዙ በጥቂቱ ከላይ በተገለጹ ገገር ምክንያች የተነሳ የዕጽዋት ዘር አዋጅን በፌደራል ተዋካዮች ምክርቤት ማጸደቁ አገራዊ መጣጣም እና በዕጽዋት ዘር አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ከመፍጠር አንጻር ፋይዳው የጎላ መሆኑ ግልጽ ነው።

## የረቂቅ ሕጉ ዓላማና ግብ

ረቂቅ ሕጉ የሚከተሉት ዓላማዎችና ግቦች አሉት።

ዓላማዎች

1. የዕፅዋት ዘር ዋስትናና ሉአላዊነትን ማስከበርና የዘር አቅርቦት በጥራት፣ በዓይነት፣ በመጠን በዘላቂነት ማረጋገጥ፤
2. የአገሪቱ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪውን ለማዘመንና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ለማስፈን ቴክኖሎጂና ኢንቨስትመንት በመሳብ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣
3. በዓለም ገበያ ተሳታፊና ተወዳዳሪ የሚያደርግ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በተለይ የግሉን ዘርፍ የሚያበረታታ የዘር ኢንዱስትሪ መገንባት፤
4. ከውጭ ሃገራት ገቢ የሚደረግ ምርትን መቀነስ፣ ወደ ውጭ ሃገራት የሚላክ ምርትን፣ እየተስፋፉ በመምጣት ላይ ላሉ አግሮ-ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ምርት ፍላጎት አቅርቦትን ማሳደግና የምግብና ሥነ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ለሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ ማበርከት፤

የሚያስችል የህግ ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት።

ግቦች

1. በምርምር፣ዘር ማምረት እና ግብይት የመንግስት፣ የግል እና የህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው የሚሳተፉ ኩባያዎች ቁጥርና አቅም ያድጋል፤
2. ከምርምር ተቋማት የተለቀቁና ወደ ምርትና ግብይት የገቡ ዝርያዎች በምርጥ ዘር ተጠቃሚዎች ዘንድ ያላቸው ተፈላጊነት እና በዝርያ ቁጥርም በምርት መጠንም አሁን ካለበት ወሳኝ በሆነ አኃዝ ያድጋል፤
3. ተጠቃሚዎች ጥራቱ የተረጋገጠ ምርጥ ዘር በዓይነት፣ በመጠን፣ በተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ እና በወቅቱ ተደራሽ የመሆን ዕድላቸው ወሳኝ በሚባል መልኩ ያድጋል፤
4. በምርታማነታቸውና ሌሎች ጠቃሚ ባሕርያቸው የተነሳ ወደ ገበያ የሚገቡ ዝርያዎች ቁጥር ስለሚጨምር የሰብል ምርትና ምርታማነት ያድጋል፤ ከውጭ የሚገባ የሰብል ምርት (ስንዴ፣ ሩዝ፣ የቅባት ሰብሎች…) በአገር ውስጥ አምርቶ ለመተካት የሚደረገው ጥረት ይጠናከራል፤ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት እና ለውጭ ገበያ የሚሆን የሰብል ምርት አቅርቦት መጠን ይጨምራል።

## የረቂቅ አዋጁ ዋና ዋና ድንጋጌዎች ማብራርያ

በዋና ዋና የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌዎች ላይ የተሰጡ ማብራሪያዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ክፍል አንድ

**አንቀጽ ሁለት፡ ትርጉም**

በትርጉም አዋጁ ክፍል ትኩረት ተሰጥቶ የተተረጎሙ ዋና ዋና ጉዳዮች ከዚህ በፊት በነበሩ ህጎች ግልጽነት ያልነባራቸውን ጉዳዮች ግልጽ የማድረግ (ዕጽዋት፣ ዝርያ መልቀቅ፣ ጥራቱ የተገለጸ ዘር..)፣ አዳዲስ ጉዳዮች በተካተቱባቸው ነባር ቃላትና ሃረጎች ይበልጥ አካታች እንዲሆኑ ማድርግ ( የዘር ትርጉም ደንን፣ የመኖ ዘርን፣ የሰብል ዘርን እንዲያካትት ተደርጎ መተርጎሙ)፣ አሁን በስራ ላይ ያለው የዘር አዋጅ አስፈላጊ ባልሆነ መልኩ ይዟቸው የቆዩ ቃላትና ሐረግ ትርጉሞች ማስወገድ፣የቃላትና ሐረጎች ትርጉም ባጠር መጠን ግን ገላጭ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ በሚያስችሉ ቦታዎች በዚህ መልኩ እንዲቃኙ ማድረግ ( አራቢ ዘር፣ ቅድመ መስራች፣ መስራችና የተመሰከረለት ዘር…)፣ አንዳንድ ትርጉሞች በሌላ አገራዊ ህግ ከተሰጣቸው ትርጉም ጋር እንዲጣጣሙ የማድረግ (ለምሳሌ ልውጥ ሕያው፣ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች፣ የአርሶ/አርብቶ አደሮች ዝርያ)፣ ሌሎች ቃላትና ሐረጎች ከዓለም አቀፍ ህጎች ጋር እንዲጣጣሙ ማደረግ ( ቅድመ እና ድህረ ቁጥጥር)፤ አሁን በስራ ላይ ባለው ህግ ያልተካተቱ አዳዲስ ቃላትን መተርጎም (ለምሳሌ የመጠባበቂያ ዘር ሥርዓት፤ራስ አገዝ የዘር ጥራት ማረጋገጥ፣ የሶስተኛ ወገን ዘር ጥራት ማረጋገጥ…)ሃገራዊ የመንግስት ስራ አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ተክትሎ የታዩ አዳዲስ አደረጃጀቶችን ሲያሚ መተርጎም( ለምሳሌ፡ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣ የክልል ባለስልጣን) የተከተለ ነው።

## ክፍል 2፡ ዝርያዎች ሥለመልቀቅና ስለመመዝገብ

**አጠቃላይ ማብራርያ**

የሰብል ዝርያ ማለት አንድ ወጥ የሆነ የማይዋዥቅ ባህሪ ያለውና በአንድ የዕፅዋት አይነቴ (Species) ውስጥ ካሉ ሌሎች ዝርያዎች የተለየ በቀላሉ ሊለይ የሚችል (Morphological)፣ ባዮኬሚካል (Quality Traits) ወይም ሞለኪውላር (Molecular Marker or DNA Finger Print) መለያ ባህሪ ያለው ነው። አንድ የሰብል ዝርያ ዘሩ በሰፊው ተመርቶ ወደ ምርት ከመግባቱ በፊት የዝርያውን ጠቀሜታና የአግሮኖሚ ብቃቱን ለማወቅ በብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ (National Performance Trial, NPT) ተገምግሞ ተቀባይነት ሲያገኝ በብሄራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ይደረጋል። የተለቀቀ ዝርያ የባለቤትነት መብት ጥበቃ እንዲደረግለት ጥያቄ ሲቀርብ የተለየ (Distinict)፣ ወጥነት ያለው (Uniform) የማይዋዥቅ (Stable) ሙከራ (DUS-test) ተካሂዶ መስፈርቶችን ሲያሟላ እንዲመዘገብ ይደረጋል።

የዝርያ ለቀቃና ምዝገባ ሥራ የሚከናወነው ዝርያው ጥቅም ላይ እንዲውል እውቅና ለመስጠት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ የስነ ምህዳር ቀጣናዎች ለተወሰኑ ወቅቶች የመስክ ሙከራዎች ይደረጋል። በብዙ አገሮች ዝርያ ለቀቃና ምዝገባ እንደ የሰብሉ ዓይነት አስገዳጅ ወይም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው።

በተጨማሪም በአብዛኛው አገሮች የዝርያ ብቃት ግምገማ ተግባራት የሚከናወነው በዝርያ ማፍለቅ ተግባር በማይሳተፍ ራሱን በቻለ ተቋም ነው። በኢትዮጵያ ለሁሉም የሰብል ዓይነቶች ዝርያ ለቀቃና ምዝገባ አስገዳጅ እና ለዝርያ ግምገማ የሚሆነው ሙከራ የሚከናወነው ዝርያ በሚያፈልቀው ተቋም ሆኖ ቆይቷል። ከዚህም የተነሳ ውጤታማ፣ አሳታፊና ታአማኒ የሆነ የዝርያ ለቀቃ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም።

በዚህ አዋጅ መሰረት ዝርያ አስቀድሞ የብቃት ማረጋጋጫ ሙከራዎችን ሳያልፍና ሳይመዘገብ በከፍተኛ መጠን ተባዝቶና ተመርቶ ለገበያ ማቅርብ አይችልም።በሌላ አባባል አገሪቱ የምትከተለው በዋነነት አስገዳጅ የዝርያ ለቀቃ ሥርዓትን ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት የምርጥ ዘር ተጠቃሚው ባብልጫ አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶአደር ስለሆነ አርሶአደሩን ከኪሳራ ለመታደግ ነው። በተጨማሪም አንድ ጊዜ የተለቀቀ ዝርያን በድግግሞሽ በማስለቀቅ የሚድርስን የሃብት ብክነትን ለመከላከል ነው። ከዚህም ባሻገር የበሽታና ተባይ ተጽዕኖ ግምገማ ሥራም ስለሚከናወን ተዛማች በሽታና ተባዮችንም መከላከል ያስችላል።

**አንቀጽ 4**

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ሙሉ በሙሉ በራሱ ሙከራ ጣቢያ ፍተሻ በማድረግ ዝርያ እንዲለቀቅ ያደርጋል ወይም አሁን በስራ ላይ ያለውን የዝርያ ሙከራን በአመልካቹ በማሰራት ማከናወን ወይም ቀጥታ ከውጭ የሚቀርብለትን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ዝርያ እንዲመዘገብ ሊያደርግ ይችላል፤ ይህ እስከ አሁን ከነበረው አሰራር በተሻለ መልኩ አማራጮችን ያመላከተ ነው። በተለይ የውጭ ሆነ የአገር ውሰጥ ምርምር ድርጅቶችን ሪፖርት በመቀበል ረገድ እምነት የሚጥልባቸው የውጭ ኩባንያዎች የሚያመጡት ቴክኖሎጂ ሪፖርት በቂ ከሆነ እና ኩባያንያው ዝርያው አሉታዊ ተጽዕኖ ቢያስከትል ተገቢውን ኃላፊነት እንደሚወስድ ሲያረጋግጥ እና በመመሪያ በሚገለጹ ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ ከውጭ በሚገቡና በተመረጡ ሰብል ዝርያዎች በባለስልጣኑ የዝርያ ብቃት ማረጋገጥ ሙከራ መስራት ሳያስፈልግ የዝርያው ባለቤት በሚያቀርበው ቢያንስ የአንድ ሥነምህዳር የአገር ውስጥ የማላመድ ሙከራ ውጤት እና የኳራንቲን መስፈርት መረጋገጡን መሰረት በማድረግ ማጽደቅ፣ መመዝገብና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊፈቅድ ይችላል። ለአንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችም ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጃል።

ባለስልጣኑ ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ብሎ ለሚያምንባቸው የሰብል ዝርያዎች በጥብቅ እርሻ ተባዝተው ቀጥታ ወደ ውጭ አገር እንዲላኩ የሚያስችል

አሰራርም ይዘረጋል፡፡ ይህን ሲያደረግ የማላመድ ሙከራ ሪፖርት አይጠይቅም፡፡ የሚጠይቀው ጉዳይ ቢኖር የኳራንታይን ኢንፖርት ፐርሚት ብቻ ይሆናል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያ ያዘጋጃል፡፡ በዋናነት አሉታዊ ተጽዕኖን ለመከላከል የሚያስችል እንዲሆን ተደርጎ መመሪያው የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ አሉታዊ ተጽዕኖው በዋናነት በአገሪቱ ያልነበሩ ግን የኳራንታይን ፍተሻ ስርዓታችንን በድንገት ሊያልፉ የሚችሉ የተባይና በሽታ ክስተቶች ለመከላከል ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡ ከዚህም ባሻገር ግብርና ሚኒስቴርና ግብርና ባለስልጣን በመመካከር ሊከተሉት የሚገባ በውጭ የተመዘገቡ እና ልዩ ፋይዳ አንዳላቸው በሚታመኑ የዕጽዋት የዝርያዎች ቀጥታ አጠቃቀም ላይ ድንጋጌ ተካቷል፡፡ ይህ ደግሞ ሚኒስቴር መ/ቤቱን ልዩ ፍላጎት በሚነሳበት ወቅት አንዲጠቀም የሚረዳው አሰራርን ለማስፈን ያግዛል፡፡

በዚህ ክፍል ሌላው ትኩረት ያገኘ ጉዳይ የብሔራዊ ዝርያ ለቀቃ ኮሚቴን ስልጣንና ተግባር ማስፋት ነው፡፡ ከዚህ በፊት ባለነበረ ሁኔታ ዝርያ መልቀቀ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያት መመረታቸው የቀሙ ዝርያዎችን ከምርት ውጭ መሆናቸውን መወሰንና ከዝርያ ምዝገባ ዝርዝር አንዲወገዱ ማድረግን አንዲሁም  የዝርያ ለቀቃን ሙሉ በሙሉ አንዲመራ የማድረግ ኃላፊነትም እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ** 5

ከዚህ በፊት ባልነበረ ሁኔታ አገሪቱ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በሌሎች አገሮች የተመዘገቡትን ዝርያዎች ተቀብሎ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በዝርያ መዝገብ እንዲካተቱ የማድረግ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ይህም አገሪቱ በዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን እያደረገች ያለችውን ጥረት እና የምስራቅ እና ደቡብ አፍሪካ የጋራ ገበያ ድርጅት(COMESA) አባል ሆና የድርጅቱን የዘር ንግድ ደንብ መቀበሏን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ የጋራ ገበያው አባል ሆና እየተንቀሳቀሰች ብትሆንም የድርጅቱን የዘር ደንብ አተገባበር መርሃ ግብር ግን በውሉ እየተተገበረ አይደለም፡፡

## ክፍል 3፡ ስለዘር ማምረት፣ ዝግጅትና ግብይት

### አጠቃላይ ማብራርያ

የዕፅዋት ዘር ማምረት ማለት ዝርያ ከተለቀቀ ወይም ከተመዘገበ በኃላ ከመነሻ ትውልድ ዘር እስከ የተመሰከረለት ዘር ያሉትን ትውልዶች ማባዛትና ማዘጋጀት ያሉትን ተግባራት ያካትተል፡፡ ምርጥ ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀትና ለተጠቃሚው ማቅረብ ብዙ ባለ ድርሻ አካላት የሚያሳትፍና የእነዚህን ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ሃላፊነት የተሞላበት አስተዋፅኦ እውን ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በአገራችን ዘር የሚመረተው በአምራች ኩባንያዎች በተያዘ ማሳ እና በአርሶአደሮች ማሳ ላይ ነው፡፡በአገሪቱ እነዚህን አካላት አቀናጅቶ መምራትና ማስተባበር በአብዛኛው ያልተሳካ ተግባር ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የመነሻ ዘርን በሚፈለገው መጠን፣ ጥራት፣ ዓይነትና በፍትሃዊነት እንዳይቀርብ በማድረግ አርሶና/አርብቶ አደሩም በፍላጎቱ መሰረት የተመሰከረለተ ዘር በጥራትና በመጠን እና በተፈለገው ጊዜ እንዳያገኝ ምክንያት ሆኖአል፡፡

የዘር ግብይት ዋና ዓላማ ትክክለኛ የግብይት  ስርዓት በመዘርጋት አርሶ/ አርብቶ አደሩን የምርጥ ዘር ተጠቃሚ ለማድረግ እና የዘር አምራቾችና ነጋዴዎች የተለያዩ የግብይት መንገዶች (marketing channel) በመጠቀም የዘር አቅርቦትን ለማሳለጥና ውጤታማ ለማድረግ ነው፡፡ ውጤታማ የዘር ግብይትና ሥርጭት አለ ማለት የሚቻለው የዕጽዋት ዘር በሚፈለገው መጠን፣ በጥራት፣ በወቅታዊነት፣ በተወዳዳሪ ዋጋ እና ልዩ ልዩ የግብይት መንገዶች (marketing channel) ተግባራዊ በማድረግ የዘር ስርዓቱ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ የዘር ግብይትና ሥርጭት

የራሱ ዋና ዋና ሂደቶች ያሉት ሲሆን የዘር ፍላጎት ዳሰሳ፤ የዘር አቅርቦት፣ ግብይትንና ሥርጭትን የሚያካትት ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ አገሮች የዘር ግብይትን በሚመለከት በዋናነት በነፃ ገበያ የሚከናወን ሲሆን በተወሰነ መልኩ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መንግስትን በማሳተፍ የሚያካሂዱ የግብይትና ሥርጭት ተግባራት ተብለው ይታወቃሉ። በአገሪቱ ይህ በዋናነት በመንግሥት እየተከናወነ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ግን የቀጥታ ዘር ግብይት ሥርዓት እየተዘረጋ ይገኛል። ሆኖም ግን ውጤታማ የግብይት ሥርዓት ባለመኖሩ ምርጥ ዘር በዓይነት፣በመጠን እና በተፈለገው ጊዜ ባለመቅረቡ የአርሶአደሩን ፍላጎት ሳያሟላ በከፍተኛ መጠን በየአመቱ እያደረ ይገኛል።

**የክፍል 3 ማብራርያ**

ዘር የሚመረተው ለመሸጥ ከሆነ ዘሩን ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውለው መነሻ ዝርያ ስም ያለው፣ ምንጩ የታወቀ፤ በሚኒስቴሩ የዝርያ መዝገብ ውስጥ የሰፈረ መሆን አለበት። ከዚህም ባሻገር በመመረት ሂደትም ከዝርያው ልዩ አረባብ ባህርይ ወይም ከማሳው የበሽታና ተባይ ታሪክ ወይም ከአጎራባች ማሳ ርቀት ጋር ተያይዞ ለብክለት ሊዳረግ ይችላል። ይህ ደግሞ የሙያ ብቃት መስፈርቶች አሟልቶ መሰማራትን ይጠይቃል። ይህን ማስፈጸም ደግሞ ለኢትዮጵያ ግብርና ባለሰልጣንና እና ለክልል ባለሰልጣን ሥልጣን የሚሰጥ የህግ ድጋፍ ሥርዓት ስላስፈለገ እንዲካተት ተደርጓል።

ስለዚህ ክፍሉ በዋናነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመያዝ፣የውስጥ ዘር ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት አስፈላጊነት፣የብቃት ማረጋገጫ የያዘ ሰው መብት፣ የዘር ማምረት ዕቅድን ለሚመለከተው የመንግስት አካል ስለማሳወቅ፣

ይህ ክፍል ማሻሻያው ከርዕሱ ይጀምራል። “ስለ ዘር ማምረትና ማከፋፈል” የነበረው የክፍሉ ርዕስ “ሥለዘር ማምረት፣ ማዘጋጀትና ግብይት” በሚለው እንዲተካ ተደርጓል። ይህም የተደረገበት ዋና ምክንያት የመንግስትን ቀዳሚ ትኩረት የነበረውን በማከፋፈል ላይ የተመሰረተውን አሰራር በመለወጥ በገበያ መርሆች የሚመራ ሥርዓት ለማስፈን የተተለመውን ግብ ለማመላከት እንዲረዳ ነው።

**አንቀጽ** 6

ይህ አንቀጽ ስለ ዘር ምርት ዕቅድ ይደነግጋል። ሰለ ዕቅድ መደንገግ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት አገራዊም ሆነ ክልላዊ አቅምንና ክፍተትን አስቀድሞ በመለየት መንግስት አማራጭ መፍትሄዎችን ለአርሰ/አርብቶአደሩ መቅረብ እንዲያችል ነው።

**አንቀጽ** 7

በዚህ አንቀጽ ስር የደንና ሌሎች ቋሚ ሰብሎች ዘር ማምረትን ባካተተ መልኩ ማንኛውም ሰው ዘር ለማምረት ከመሰማራቱ በፊት የማምረቻን ቦታ ማስመዝገብንና የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት። ከዚህ በፊትም ባልነበረ ሁኔታ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስራች/የተመሰከረለት ዘር አምራችና በቅድመ መስራች ዘር አምራች ደረጃ እንዲከፋፈል ተደረጓል። ይህም ድንጋጌ ያስፈለገበት ምክንያት የቅድመመስራች ዘር አጠቃቀም ብቃትን በማሳደግ ብክንትን ማሰወገድና በዚህ ረገድ የመሚታየውን ዕጥረት መቀነስ ነው። ሁሉም ከሚወሰደው ይልቅ አቅም ያላቸው እንዲያመርቱት በማድርግ የሃብት አጠቃቀምን ማሳደግ ነው።

የመነሻ ዘር ለተመሰከረለት ዘር ማመረት ቁልፉ ግብዓት ነው። እንደ ግብር ከፋይ የተመሰከረለት ዘር አምራች የተመዘገቡ የመንግስት ዝርያዎችን መነሻ ዘር ከመንግስት ምርምር ማዕከላት የማግኘት መብት አለው። የመነሻ ዘር ደግሞ ለሙሰና ተጋላጭ ከሚባሉ የመንግስት ሃብቶች አንዱ እየሆነ መጥቷል፤ ዘር አምራቾችም ከፍተኛ የሆነ

ቅሬታ ከሚያቀርቡበት ግብዓት አንዱ ነው። ስለዚህ ይህን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያ እንዲያወጣ የህግ አውጭው አካል ለግብርና ሚኒስቴር ሥልጣን እንዲሰጠው የቀረበ ጥያቄ ነው።

እስከቅርብ ጊዜ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከምርምር ማዕከላት ሳይቀር የሚመረቱ ዝርያዎች ዘር የተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማረጋገጫ ሳያገኙ በሙከራ ላይ ያሉ ዝርያዎችን ዘር ለዘርነት እያባዙ ለሽያጭ ሁሉ እንደሚያቀርቡ ተረጋግጧል። ይህ ብቻ ሳይሆን ምንጫቸው የማይታወቅ ዝርያዎች እየተዘሩ ለከፍተኛ ተዘማችና ኳራንቲን ተባዮችና በሽታዎች መስፋፋት ምክንያት ሆኖ ተስተውሏል። ለመጥቀስ የማንጎ ነጭ ስኬል ማንጎ ላይ፣ በትግራይ የተከሰተው የበለስ ተክል በሽታ፣ በዚሁ ክልል የተከሰተው የተፈጥሮ ወይራ በመጤ በሽታ መጠቃት፣ በደቡብ በዝንጅብል ላይ የተከሰቱ አዳዲስ በሽታዎችን እንደ ዋቢ መውሰድ ይቻላል። ስለዚህ አምራቾች ወደ ማምረት ከመግባታቸው በፊት የሚያመርተውን ዘር ምንጭ፣ ዘር ደረጃና ሌሎች የጥራት መስፈርቶችን ለክልል ባለስልጣን የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው።

በዚህ አንቀጽ ስር የተካተተው ሌላላ ድንጋጌ ደግሞ የግብርና ውልን ተጠቅመው ዘር ስለሚያመርቱ ዘር አምራቾች የተመለከተው ነው። የአርሶአደር ማሳ ላይ በውል ተመስርቶ የሚካሄድ የዘር ማምረት ፕሮግራም የአምራቾች ዋና የማሳ ፍላጎትን የሚያሟላ ነው። ይህን ማሳ በውል ተመሰርተው እንደሚጠቀሙ በመጥቀስ የንግድ ሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲጠይቁ የራሳቹህ ማሳ ሊኖራቹህ ይገባል ስለሚባሉ በዘርፉ የሚደረገው ኢንቨስትመንት እንዲቀጭጭ አድርጎታል። ይህ ድንጋጌ ለኢንቨስተሮች በዘር አምራችነት እንዲመዘገቡ ባመበረታታት ተሳተፎአቸውን ያሳድጋል። ከዚህም በተጨማሪ በአርሶአደር ዘር ብዜት ተሰማርተው የሚሰሩ አምራቾች የተመረተን ዘር በማስመለስ ረገድ ከፍተኛ ተግዳሮት እየገጠማቸው መሆኑን ይናገራሉ። አስገዳጅ ሥርዓት ባለመኖሩ አርሶአደሮች ዘር ካመረቱ በኋላ በውላቸው መሰረት ለአምራቾች ያለመመለስ ችግር ስላለ በዚህ የተነሳ በከፍተኛ ወጪ የተመረተ ዘር ለተፈለገበት ተግባር ሳይሆን ለምግብነት ወይም ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት ሲሸጥ በተደጋግሞ ተስተውሏል። ሥለዚህ ህግ አውጭው አካል በኮንትራት ላይ የተመሰረተ የዘር ብዜት ላይ ዝርዝር መመሪያ እንዲያወጣ ሥልጣን እንዲሰጠው ይረደዋል።

**አንቀጽ** 9 **እና** 10

የግብይት ዓይነቶችን በመደንገግ የሚጀምረው አንቀጽ የብቃት ማረጋገጫ አስመልክቶ የክልሎችና የፌደራልን ኃላፊነት በግልጽ ይደነግጋል። አምራቹ በክልል ብቻ ተወስኖ የሚሰራ ከሆነ ከክልል ባለስልጣን ፤ ክልል ተሻጋሪ የሆነ ግብይትን መሰረት ያደረገ ማምረት የሚያከናውን ከሆነ ግን ከኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ያገኛል። ከዚህም በተጨማሪ የመንገስት ዝርያዎችን ተጠቅሞ ዘር ማምረትን የሚያከናውን የህዝብ ሃብት የሆኑ ዝርያዎች ሲጠቀም እንደ ማህበራዊ ግዴታው ዕቅድ ይዞና ከምርምር ተቋማት ጋር እየተመካከረ አዳዲስ ዝርያዎችን የማስተዋወቅ ስራ መስራት አለበት። ይህም አንዱ ሌላው በሰረው የማስተዋወቅ ስራ እየገባ ገበያ መሻማትን ከማሰወገዱ በተጨማሪ ሁሉም ሲሳተፍ ያየ አምራች ተበረታቶ ዝርያዎች እንዲያስተዋውቅ ያደርጋል። ስለዘዚህ የአርሶአዶሮች እውቀት ይጨምራል። የተሻሻሉ ዝርያዎች የመጠቀም ፍላጎትም ያድጋል። ፍላገቱም ሲያደግ የግብይቱ ተደራሽነትም እንዲያድግ ዘር እንደቀድሞ በመንግስት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አቅራቢዎች እንዲከናወን ድንጋጌው ያግዛል። ስለዚህ ብዙ የግብይት አማራጮችም እንዲካተቱ ተደርጓል።

ከዚህ በፊት በነበሩ ልምዶች በመመስረት አንድ ሰው የግብይት አድማሱን ከአንድ ክልል በላይ ለማስፋት ከፈለገ ክልሉ የሰጠውን የብቃት ማረጋጫ በመመለስ አዲስ ሰርተፊኬት ከኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ማግኘት አለበት።

**አንቀጽ** 11 **እና** 12

የመረጃ ሥርዓታችን በማሻሻል ጠቃሚ ወደ ሆነ ትንተና መለወጥ ያስፈልጋል። ከእነዚህ ትንተናዎች ውጤት በመነሳትም በቀጣይ ምርት ዘመን የምርጥ ዘር አገራዊ የአቅርቦት አቅማችንን ማሳደግ የሚያስችሉ ምክረ ሃሳቦችን

ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል። ከእነዚህም ማስፈጸሚያ መሳሪዎች አንዱ የመጠባበቂያ የዘር ሥርዓት መዘርጋት ነው። እስከአሁን የነበረው የግምገማ ድጋፋችን የዘር እጥረት እንደነበር የሚገልጽ እንጂ ወሳኝ በሚባል መልኩ ክፍተቱን ማስተዳደርና መምራት የሚያስችል አገራዊ አቅም የለንም። በርግጥ ይህ አሰራር ከሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት የሚከናወን ይሆናል። ይህንን ዝርዝር የሚደነግግ ደንብ ይዘጋጃል። በሚኒስትሮች ምክር ቤት ድንብ እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት ከአንድ በላይ የሆኑ የመንግስት ተቋማትን ስሚያሳትፍ ነው። የሥርዓቱ ዋናው ጽንሰ ሃሳብ በመልካም ዓመታት የሚገኘውን የተትረፈረፈ ምርጥ ዘር ሰብስቦ በማስቀመጥ በቀጣይ ዓመታት ከአርሶአደሩ ፍላጎት ጋር መቀያየር ጋር ተያይዞ የሚመጣን ልዩ የገበያ ፍላጎት ማስተናገድ የሚችል አቅም መፍጠር ላይ ያተኮረ ነው። እጥረት በሚከሰትበት ዓመት የአደጋ ግዜ ዘር ከመጠቀም ያድናል። እስከአሁን ባለው ልምድ እስከ 400000 ኩ/ል ምርጥ ዘር አስከማድር የደረሰበት ዓመት ነበር። ይህ ያደረ ዘር ባብዛኛው በእህልነት የሚሸጥ ሲሆን የተወሰነው መጠን ደግሞ በየወረዳውና ሕብረት ስራ ማህበራት መጋዘኖች እንዳለ ተበላሽቶ ተወግዷል ወይም መጋዘን እንደያዘ አለ። በዚህ መልኩ የሚባክነው የህዝብ ሃብት በሚሊየኖች የሚገመት ነው። ግን ሥርዓት አበጅተን ዘሩን በአግባቡ ቢያዝ እስከ አምስት ዓመታት ድረስ ቀዝቃዛ ቦታ በማስቀመጥ የዘር አቅርቦት ዋስትናን ማረጋገጥ ይቻላል። ይህ ደግሞ ተረቀ በቀረበው ፖሊሲ ተካቷል። ስለዚህ ህግ አውጭው አካል የችግሩን አሳሳሳቢነት በማየት ለሚኒስቴሩ ይህን ሥርዓት መዘርጋት እንዲችል ሥልጣን እንዲሰጠው የተካተተ ነው።

## ክፍል አራት፡- ጥራት መቆጣጠርና ማረጋገጥ

### አጠቃላይ ማብራርያ

ዘር ህይወት ያለው በመሆኑና የሚቀጥለውን ትውልድ ውጤታማነት ስለሚወስን ዘርን በጥራት ማምረት፣ በአግባቡ መንከባከብና ከድህረ ምርት በኋላ በጥንቃቄ መጓጓዝ፣ መዘጋጀት፣ መከማቸትና መሰራጨት ይኖርበታል። የዘር ጥራትን ማረጋገጥ ማለት አንድ የተለቀቀና የተመዘገበን ዝርያ ከቅድመ መሰራች እስከ ተመሰከረለት የዘር ትውልድ ድረስ የአገሪቱን የማሳና የላቦራቶሪ የጥራት መስፈርቶችን አሟልቶ ስለመመረቱ ማረጋገጫ የሚሰጥበት ሂደት ነው። ዘርን በጥራት የማምረት ተግባር የአምራቹ ኃላፊነት ሲሆን ይህንን ማረጋገጥ ደግሞ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት ተቋም ወይም አካል ኃላፊነት ነው። በአንዳንድ አገሮች የጥራት ማረጋገጥ ሂደት አገልግሎቶች ለሦስተኛ ወገን በማስተላለፍ የሚሠራ ሲሆን የመጨረሻ ማረጋገጥ ግን አግባብ ያለው የመንግሥት አካል ኃላፊነት ነው። ይሁንና በኢትዮጵያ እስካሁን እነዚህ ባለመተግበራቸው ደረጃውን የጠበቀ ጥራት ያለው ዘር ለተጠቃሚው ማቅረብ አልተቻለም። በመንግስም ከፍተኛ የሆነ የበጀት ጫና እየፈጠረ ይገኛል።

## የክፍሉ ማብራርያ

**አንቀጽ** 13

የዓለም አቀፍ ልምዶች የሚያመለክቱት የዘር ጥራት ማረጋገጥን ባብዛኛው የሚከናወነው በመንግስት አካል ነው። ይህ ደግሞ ደረጃ ከማውጣት ይጀምራል። ደረጃዎች ተግባራትን በተጣጣመ መልኩ ለመምራት ፋይዳቸው ጉልህ ነው። የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 እንደሚያትተው የፌደራል ባለስልጣን መ/ቤቶች ደረጃ እንደሚያውጡ ይደነግጋል። ስለዚህ በዚህ አዋጅም ይህን ስልጣን  በዘር ዘርፉም ተግባራዊ ማድረግ ያስችል ዘንደ ረቂቅ ድንጋጌ ተካቷል።

**አንቀጽ** 14

በዘር ጥራት ማረጋገጥ ቁልፍ ተቋማት የሚባሉት የዘር ላቦራቶሪዎች ናቸው። በማናቸውም በዘር ዘርፉ የተሳካላቸው ሃገራት የዘር ላቦራቶሪዎች ዓለምአቀፍ እውቅና እዲያገኙ ያደርጋሉ። ከዚህ የተነሳ ከዓለም አቀፍ ገበያዎችን ተጠቃሚ አንዲሆኑ አደርጓቸዋል። በአገራችን ግን ይህን ለማድረግ ለአስርት ዓመታት ጥራት ቢደረግም በመደበኛ መልኩ አባል መሆን አልተቻለም። ስለዚህ እነዚህን ላቦራቶሪዎች  በአገር አቀፍ እና አለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ መንግስት የህግ ድጋፍ እንዲኖረው የሚያስችል ድንጋጌዎችም ተካተዋል።

**አንቀጽ** 15፡ **የዘር ኢንስፔክሽን**

እንደሚታወቀው ዘር የሚመረትበት ማሳ ያለው ክልል መንግስታት ሥር ነው። ለኢንፖርትና ኤክስፖርት የሚሆነውን ዘር ጥራት የመቆጣጠር ኃላፊነት ደግሞ ያለው በሚኒስቴሩ ጥላ ሥር ነው። ስለዚህ የሁለቱን መንግስታት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥን አስመልክቶ ሊኖራቸው የሚገባን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተቀምጧል። ሌላው ደግሞ ህገ መንግስቱ ለፌደራል መንግስት ስለ ስታዳርዳይዜሽን የሰጠውን ሥልጣን መሰረት በማድረግ ሃገራዊ የዘር  ኢንስፔክሽን አሰራር ወጥነት ለማስፈን የሚያስቸለውን ድንጋጌ ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ የህግ ማዕቀፎች ለመፈጸም የሚያስችል ባለሙያዎች መሰየም ስልጣን ስልሚጠይቅ ምክር ቤቱ ይህን ስልጣን እንዲሰጥ የሚሰየሙ ባለሙያዎችን ዝርዝር ድንጋጌ ቀርቧል።

**አንቀጽ** 16፡ **የዘር ጥራት ማረጋገጥ**

የዘር ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በመንግስት ከሚከናወንበት አሰራር በተጨማሪ ወጪውን ሊጋሩለት የሚችሉ አሰራሮችን በስርዓቱ ውስጥ ማስገባት እንዲቻል ይህ አንቀጽ ያትታል። የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥራ ከሚጠይቀው ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ አኳያ ክልሎች ይህን እንዲያሟሉ ከመገፋፋት ይልቅ የፌደራል እና ክልል መንግስታት ወጪያቸውን የሚያቃልሉበትን ስልት ማቅረቡ እንደ አማራጭ መፍትሄ ቀርቧል። በዘር ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት ረገድ ባለፉት ሁለት አሰርት ዓመታት በምርጥ ዘር ጥራት አጠባበቅ ስልታቸው በአርሶአደሮችም ሆነ በማሳ በሚታይ ማሰረጃ የተደገፈ መልካም ስም ያተረፉና የተመሰከረላቸውን የዘር አምራችና ግብይት ድርጅቶችን እውቅና መስጠት ይገባል።ይህን እውቅና መስጠት የተቀጣጣሪውን ባለስልጣን መገኘት ሳይጠብቁ ራሳቸው የዘር ምርት ጥራት አረጋግጠው የሚሸጡበትንና የመንግስትን ወጪ የሚጋሩበት ሥርዓት እንዲዘረጋ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።በተጨማሪም ምርጥ ዘር በወቅቱ ለአርሶአደሮች እንዲያቀርቡ ይረዳቸዋል። ሥርዓቱን ለመዘርጋት ደግሞ የህግ አውጭውን ይሁንታ ማግኘት ይገባል። ይህን ለመተግበር የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱት የክልል ባለስልጣን መ/ቤቶች ይሆናሉ። ምክንያቱም ሥራው ያለው በክልሎች መሬት ነውና። የግብርና ባለስልጣን ድርሻ የሚሆነው ሥርዓቱን መምራት የሚያስችል መመሪያ  እንዲወጣ ማድረግ እና ድጋፍ መስጠት ይሆናል።

**አንቀጽ** 17፡  **የዘር ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**

**አንቀት** 18፡ **.የዘር ጥራት ማረጋገጫ መለያ ምልክት ስለማድረግ**

በዚህ ዓይነት የምስከር ወረቀት አሰጣጥ ላይ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣንና የክልል ባለስልጣን ኃላፊነትና ተግባር በግልጽ ተቀምጧል። በእነዚህ አንቀጾች ስር የሰፈሩ ድንጋጌዎች ማስፈር ያስፈለገበት ምክንያት የተግባርና ኃላፊነት ግጭትን በማስወገድ ሥራዎች በተሳለጠ እና ደንበኞችን በማያንገላታ መልኩ ለመምራት ስለሚረዳ ነው። ከዚህም ባሻገር ከህገወጥ መለያ ምልክት አደራረግ ጋር ተያያዥ የሆኑ ግድፈቶች በግልጽ በማስቀመጥ ህገ ወጥ አሰራሮችን ለመቆጣጠር በሚደረገው ጥረት ለህግ አስፈጻሚው አካል የህግ ክፍተት እንዳይኖር ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

**አንቀጽ** 19፡ **ቅድመ እና ድህረ ቁጥጥር**

ከትርጉም ጀምሮ ስለ እነዚህ ሃረጎች ግልጽ ድንጋጌ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። እነዚህ ሙከራዎች የጸደቀ ዘር ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ። ተግባራዊ ሲሆኑም ዓላማ አላቸው። ኢንስፔክተሮችም ሆነ የላቦራቶሪ አናሊስቶች በህግ የተሰጣቸው የመወሰን ስልጣን እጅግ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ አሰራራቸውን የሚገመገምበት ሥርዓት መዘርጋት ይገባል። ምክንያቱም ኢንስፔክተሮች በመስክና የላቦራቶሪ አናሊስቶች በላቦራቶሪ ከተቀመጠው የዘር ጥራት ደረጃ ውጭ ዘር እንዲጸድቅ ወይም እንዲወድቅ ሊያድርጉ ይችላል። ይህም በሙስና ወይም የዘሩን ባህርያት ካለማወቅ ወይም ከሙያ ብቃት ማነስ የተነሳ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የቅድመ እና ድህረ ጥራት ቁጥጥር ስራዎች በሙከራ ጣቢያ ተደግፈው የሚሰሩ ከመሆናቸው አኳያ የጥራት ቁጥጥር ሂደቱን ከመከታተልና ከመገምገም አኳያ ሚናቸው የጎላ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ባለስልጣን መ/ቤቶች በሚሰጡት ውሳኔ ቅሬታ ያለውን ሰው ቅሬታ በጥናት ለመለየት ያስችላሉ።ስለሆነም ከፍተኛ የሆነ ወጪ ይጠይቃሉ። ይህን በዋናነት ክልሎች የሚሰሩት ቢሆንም ሥርዓቱን ለመዘርጋት የግብርና ባለስልጣንም ድርሻ ይኖረዋል። ስለዚህ ሥርዓቱን ለመዘርጋት የህግ አውጭው አካል ይሁንታ ካለው  የክልል መንግስታት ተገቢውን ትኩረት ሊሰጡና ሃብት ሊመድቡ ይበረታታሉ።

**አንቀጽ 20፤የዘር ጥራት ደረጃ ስለማያሟላ ዘር**

የዘር ጥራት የማያሟላ ዘር በምን መልኩ ጥቅም ላይ እንደሚውልና ጎጂነት ባህርይ ካላው ደግሞ ምን መሆን እንዳለበት ለደንበኞችና ለዘር ጥራት አረጋጋጭ እና የህግ ባለሙያዎች አቅጣጫ ለመስጠት የቀረበ ነው። ሆኖም ግን ተግባሩ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ስለሚሻ ጉዳዩ በመመሪያ በዝርዝር ይደነገጋል።

**ከአንቀጽ 21 እስከ 25 ያሉ ደንጋጌዎች**

ብዙም ለውጥ ሳይደረግባቸው ከነባሩ ህግ ማለትም የዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 የተወሰዱ ናቸው።

**አንቀጽ 26፡ ስለ ትብብር**

ይህ አንቀጽ ከአዋጅ 782/2005 የተወሰደ ቢሆንም የተጨመረው በትብብር ስለ ሚያከናውኗቸው የማበረታቻ ተግባራት ነው።

**አንቀጽ 26-31**

እነዚህ አንቀጾች ከነባሩ አዋጅ ላይ የተወሰዱና ብዙም ለውጥ ያልተደረገባቸው በራሳቸውም ገላጮች ናቸው።